

አሰፋ ተፈሪ ንጉሴ ሲባል ስሜ
በቅድመ አያቴ በአዘነጋሽ መንገሻ ተሰይሜ
በጎንደር ልደታ ማርያም ልክ የገና ለት ተወልጄ
ለመጀመሪያ ትምህርቴ ደብረ ሰላም ማርያም ሄጄ
ሁለተኛውን በጎንደር ፋሲለደስና ደብረ ማርቆስ አገባድጄ
ብዙ ብዙ ዘምቼ ....አያሌ ቁምስቅል አይቼ
የሶስተኛውን ትምህርት ከናንተ ጋር ዓለማያ ገብቼ

አሶሳ ሚባል ቦታ ለአምስት ዓመት ምርምር ሰርቼ
በማስትሬት ዓለማያ እንደገና ጨረስኩና
ተመልሼ ባኮና አዴት ምርምሩን ሰራሁና
አምላክ አራት ልጆችን ባርኮ ሰጥቶኝ
ዛሬማ የልጅልጅ ለማዬትም አብቅቶኝ
ልጆቼን ላሳድግ ወድጄ ወደ አሜሪካ ተሰድጄ
በዋሽንግተንና ሜትሮ እስቴት ዩኒበርሲቲዎች ለነርስነት ሙያ ሄጄ
የድሮ ፍላጎቴን የመርፌ ወጊነቴን ትንሽም አለፍ ብዬ እየሰራሁ
በተጓዳኝ የተከፉ የተቸገሩ የተጠሙ ወገን በምለው እየረዳሁ
የተውኳትን የተሰጠችኝን ጽሁፍና ግጥም እያደራሁ
እጅግ ደስ እያለኝ  በተሰጠኝ ረክቼ ይኸው አለሁ።